# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

## የዕለቱ ምስባክ

አግረረ ለነ አህዛብ ወሕዝበ ታህተ እገሪነ
ወኀረየነ ሎቱ ለርዕስቱ
ሥኖ ለያዕቆብ ዘአፍቀረ

ወገኖቹን (ሕዝብ አህዛብን) ከእግራችን በታች አስገዛልን)
ለርስቱ እኛን መረጠ
የያዕቆብን ውበት የወደደ
መዝ ፵፮፤፫-፬

ትርጉም፥ ሐዋርያትና ሰባ አርድዕት «ምዕመናነ-አህዛብን ምዕመናነ-እስራኤልን በእጃችን ጭብጥ፣ በእግራችን ርግጥ አድርጐ አስገዛልን» ይላሉ። ርስት ሊሆነን ርስት ልንሆነው መንግስተ ሰማያትን ሊያወርሰን የመረጠን የያዕቆብንም ምግባር ሃይማኖት የወደደ፣ የያዕቆብን ሥጋ ለመዋሃድ የወደደ እርሱ ነው።

**ወንጌል፥** ዮሐ ፬፤፩-፳፯
**ቅዳሴ፥** የጌታችን (ነአኩተከ)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ወብዙኀን ኖሎት መጽኡ ...
(ብዙ እረኞች መጡ ... )

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፩፤፩-፲፯ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ጴጥ ፱፤፳ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፲፩፤፩-፲፱ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### ብዙ እረኞች ያላነሱት ድንጋይ

የእግዚአብሔር ሰው ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወደ ካራን ሲጓዝ መሸቶበት በመንገድ አድሮ የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ እግዚአብሔር እንደማይለየው ቃል ገብቶለት የጀመረውን ጉዞ ከአምላክ ጋር እንዲጓዝ ተስፋ ከፈጣሪ ከተቀበለ በኋላ ወደ ሩቅ ምሥራቅ አገር ሰዎች ደረሰ፤ በሜዳም ሆኖ ጉድጓድ አየ፤ ጉድጓዱም የውሃ ጉድጓድ ነው። የዚያች አገር ሰዎች በጎቻቸውም ውሃ የሚያገኙት ከዚያ ነበር። በጉድጓዱ አፍ ላይ የተገጠመው ድንጋይ በጣም ትልቅ ስለነበር ማንኛውም እረኛ እንደደረሰ ድንጋዩን አንስቶ ውሃውን ለበጎቹ ማጠጣት አይችልም ነበር።

የአገሩ እረኞች ተሰብስበው ለሃምሳ ለስልሳ ሆነው ከጉድጓዱ አፍ ድንጋዩን ገፍተው በጎቻቸውን ያጠጡ ነበር ከዚያም መልሰው ይዘጉት ነበር። ያዕቆብ በአካባቢው ያሉትን እረኞች ከየት የመጣችሁ ናችሁ ቢላቸው የካራን ነን አሉት። አጐቱን እንደሚያውቁት ቢጠይቃቸው አዎን አሉት። እንዲያውም ልጁ ራሔል በጎችዋን ይዛ ወደ ውሃው እየመጣች መሆኑን ነገሩት። ያዕቆብም የአጎቱን የላባን ልጅ ራሔልን ከበጎችዋ ጋር ባየ ጊዜ አለቀሰ፤ እርስዋንም ሳማት። ከዚያ በኋላም ብዙ እረኞች ተሰብስበው ድንጋዩን መክፈት ስለማይችሉ የሌሎችን እረኞች መምጣት ይጠባበቁ ነበር። ያዕቆብ ግን ብቻውን ያንን ድንጋይ ከጉድጓዱ አፍ ገልብጦ የአጐቱን የላባን በጎች አጠጣ፤ ያዕቆብም ለራሔል የአባቷ ዘመድ አጐቷ መሆኑን ነገራት፤ እርሷም ሄዳ ለአባትዋ ነገረችውና ወደ ቤቷ ወሰደችው (ዘፍ ፳፱፤፩-፲፬)። ይህም ታሪክ ይገለጥ ዘንድ ላለው ለኢየሱስ ክርስቶስ (የእረኞች አለቃ) አስተርዕዮ ምሳሌ ነበር። ቅዱስ ያሬድ ይህንን ሲተረጉም በዛሬው መዝሙር ሰምተናል።

የመዝሙሩ ዘር በግዕዝ
ወብዙኀን ኖሎቱ መጽኡ አስዕኑ ከሢቶታ ለዕብን እምአፈ አዘቅት እስከ ይመጽእ ያዕቆብ ዝክቡት ውስተ ኀቄሁ ዘሀሎ ይሠኀ እምሰብዕ ከሠተ ወአስተርአየ መርዔቶ ወከማሁ መጽኡ ብዙሃን ነቢያት ወሰዕኑ ከሢቶታ ለጥምቀት እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ እምሰማይ ከሠተ ወአጥመቀ ብዙኀነ አሕዛበ በውስቴታ መንክር ተአምሪሁ ለመድኃኒነ።
ትርጉም
«ብዙ እረኞች መጡ ከጉድጓድ አፋፍ ድንጋይን ግን መክፈት (መገልበጥ) አልሆነላቸውም ከሰው የሚሆነው ጌታ በአብራኩ ያለ ያዕቆብ እስኪመጣ ድረስ፤ እሱ ከፍቶ መንጋውን አጠጣ። እንደዚሁ ሁሉ ብዙ ነቢያት መጡ፤ ጥምቀትን መመስረት አልሆነላቸውም ደገኛው እረኛ ከሰማይ እስኪመጣ ድረስ፤ ሥርዓተ ጥምቀትን መሰረተ፤ ብዙ አህዛብን አጠመቀ የአምላካችን ተአምሩ ድንቅ ነው» የሚል ነው።

ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ እንዳስተማረን ድህነተ-ዓለም ሕይወተ ዓለም፣ ጽድቀ ዓለም፣ ክብረ ዓለም የተገለጠው ለሰዎች የተሰጠው የመርገም ድንጋይ የተወገደው በነቢያት፣ በካህናት፣ በጻድቃን (መዝራዕተ ጽድቅ ኲርናአ ጽድቅ) የጽድቅ ክንድ ሳይሆን ከሰማይ በመጣው እረኛ በመለኮታዊ እረኛ ነበር። አብርሃም ያልገፋው የያዕቆብ አቅም ያልቻለው በሰው ድካም ያልተወገደው የአዳም የሔዋን መርገም በእርሱ ተወገደ፤ ሃብተ ወልድና ስመ ክርስትና የተገኘው በክርስቶስ ነው። ወደ ዓለም የተላኩ ብዙ እረኞች ነበሩ። ነገር ግን ከሕይወት ውሃ ላይ የተጋረደውን የመርገም ድንጋይ ማስወገድ አልቻሉም፤ በጎቹ ከሕይወት ውሃ ተከልክለው ድንጋዩም ብዙዎችን አስጨንቆ እረኞችም እየተጉላሉ አቅም ያለው ሰው ጠበቁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣልን በጎቹ የእረፍትን ውሃ አገኙን።

ወንጌልን ከማመንዋ በፊት ባለማወቅ ሳምራዊቷ ሴት ሰማያዊውን እረኛ «አንተ ከያዕቆብ ትበልጣለህን? እርሱም በጎቹም ከዚህ ጠጡ» አለችው። ኢየሱስ ክርስቶስም «ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ይጠማል እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ሁለተኛ አይጠማም» አላት።

በወንጌለ ዮሐንስ እንደተጻፈልን ሰማያዊው እረኛ ደክሞ በጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። ከሰማርያም አንዷት ሴት ውሃ ልትቀዳ መጣች፤ ኢየሱስም «ውሃ አጠጪኝ» አላት። እርሷ ግን «እንዴት ትለምነኛለህ» አለችው። እውነተኛው እረኛም «የእግዚአብሔር ስጦታ ውሃ አጠጪኝ የሚልሽን ማን እንደሆነ ብታውቂ አንቺ ትለምኚው ነበር። የሕይወትንም ውሃ ይሰጥሽ ነበር» አላት። ሴቲቱም «መቅጃ የሌለህ የሕይወት ውሃ ከየት ታገኛለህ ይህን ጉድጓድ ከሰጠን ከያዕቆብ አንተ ትበልጣለህን? እርሱም ልጆቹም ከዚህ ጠጥተዋል።» አለችው። መለኮታዊው እረኛም «ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሁለተኛ ይጠማል እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘለዓለም አይጠማም እኔ የምሰጠው ውሃ ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ የውሃ ምንጭ ይሆናል አላት።

አንባቢ ሆይ፥
አንተስ በያዕቆብ እና በክርስቶስ መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት ታውቃለህን? ያእቆብ ካዘጋጀው ጉድጉድ የበለጠ የሕይወት ውሃ መዝገብ እንዳለውስ ልብ ብለሃልን? ከውስጥህ የማይደርቅ የሕይወት ውሃ የሚሰጠው እውነተኛ እረኛ በጎቹን በለመለመ መስክ በእረፍት ውሃ የሚያሰማራ እረኛ ነው። ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ለሰው የማይቻለው ለእርሱ ብቻ የሚቻለው ለሰው ያቃተው ለእርሱ ብቻ የሚሆንለት መዳናችንን ብቻውን ላደረገ፤ አዘቅቱን ብቻውን ለከፈተ፤ መጥመቂያውን ብቻውን ለረገጠ፤ ሰዎችን ለመፍጠርም ሆነ ለማዳን ማንም ያልተጋራው፤ ለሕይወት ውሃ ምንጭ፤ ለበጎች እረኛ ለክርስቶስ ምስጋና ይሁን።

ካህናቱና ሌዋውያኑ ያላነሱትን ቁስለኛ ሕይወታችንን ላነሳው ሳምራዊ (ክርስቶስ) ምስጋና ይግባው። (ሉቃ ፲፤፴-፴፯)

ጥቅስ፥ ወአልቦ ካልዕ ሕይወት በዝየሐይው ወአልቦ ካልዕ ስም በታህተ ሰማይ ዘይትወሐበ ለእጓለ እመሕያው (የሐዋ ሥራ ፬፤፲፪)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።